www.abyssinialaw.com




| 12ኛ አመት ቁጥር 9<br>12th Year No 9 | ባህር ዳር ጥቅምት 9 ቀን 1999 ዓ.ም<br>Bahir Dar 19th , October 2006 |
|---|---|


# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 12.75 Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box |



| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 47/1999 ዓ.ም | Regulation No.47/2006 |
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኮምቦልቻ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State Combolcha Agriculture Technical and Vocational Education and training College Establishment, Council of Regional Government Regulation. |


## ደንብ ቁጥር 47/1999 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኮምቦልቻ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

## REGULATION NO. 47/2006

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF COMBOLCHA AGRICULTURE TECHNICAL AND VOCATIONAL EDUCATION AND TRAINING COLLEGE IN THE AMHARA NATIONAL STATE

www.abyssinialaw.com



ግብርና ለክልላችን ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ከመሆኑም በላይ በገጠሩ አካባቢ ለሚኖረው አብዛኛው ህዝባችን ዋነኛው የኑሮ መሠረት በመሆኑ፣

ይህን እንጂ ይኸው ክፍለ-ኢኮኖሚ ባለፉት መንግስታት ትኩረት ተነፍጎት የቆየና ኋላቀር የአመራረት ዘዴን የሚከተል ከመሆኑ የተነሳ በኢኮኖሚው እድገት ውስጥ የሚፈለገውን ያህል አስተዋፅኦ እንዳላበረከተ በመታመኑ፤

ክፍለ ኢኮኖሚውን ተብትቦ ከያዘው ኋላቀር የአመራረት ዘዴ አላቆ ወደ ዘመናዊና ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገርና በኢኮኖሚው እድገት ውስጥ የላቀ ሚና እንዲጫወት ለማስቻል ከወቅቱ ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት ጋር ሊጣጣሙ የሚችሉ የአሠራር ዘዴዎችንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም የሚያስችል ዕውቀትና ክህሎት የጨበጠና የሰለጠነ የሰው ሃይል መኖር እንዳለበት በቂ ግንዛቤ ተይዞ ሥራው በሀገር አቀፍ ደረጃ በተማከለ አኳኋን ሲከናወን ከቆየ በኋላ ይህንኑ አላማ ለማሳካት በየአካባቢው ተቋቁመው በፌዴራሉ መንግስት ሥር ሲመሩና ሲተዳደሩ የነበሩት የግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ወደ ክልሎች ተዛውረው እንዲያገለግሉ የተወሰነ በመሆኑ፤

ይህንኑ መነሻ በማድረግ በክልላችን ከሚገኙት አንዱ የሆነውን የኮምቦልቻ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ በክልሉ አስተዳደር ስር ለማዋል የሚያስችል የማቋቋሚያ ህግ ማውጣትና ተጠሪነቱንም ሆነ ዝርዝር ተግባሩን በመወሰን እንደገና ማደራጀት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, besides being the backbone of our Region's economy, agriculture is the main basis of living for our majority of people who dwell in the countryside;

WHEREAS, provided, however, that such an economic-sector had been deprived of proper attention and pursued backward harvesting system, it, to that effect, has been believed that it has not contributed as such in the development of the economy.

WHEREAS, being fully aware of that there shall exist a manpower who is qualified and acquired knowledge and skills that enables him to utilize new technologies and working mechanisms that harmonize with the current economic needs; by exorcising the sector-economy from obsolescent harvesting system with the view to playing its best role in the development of economy and promoting same to modern and the best level, after the task has been carried out at the national level in a centralized manner, it has been determined that the Agriculture Technical and vocational Training colleges which were established in varies localities and directed and administered by the Federal Government to be transferred to the respective regions and serve with the view to meeting this objective hereof.

WHEREAS, taking this initiative into account hereof, it has been found appropriate to issue an establishing law which enables the Combolcha Agriculture Technical and Vocational Education and Training College, which is one among the colleges found in our region, to bring about its administration under the region and reorganize through the determination of both its accountability and specific duties.

www.abyssinialaw.com



የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በተሻሻለው የክልል አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 120/1998 ዓ.ም አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 14 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the power vested in it under the provisions of art. 58, sub-art 7 of the revised Regional Constitution and art.16 sub-art 14 of the revised Regional State Executive organs Re-establishment, Organization and Determination of their powers and duties proclamation No. 120/2006, hereby issues this regulation.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

## PART ONE
## GENERAL

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኮምቦልቻ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 47/1999 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Combolcha Agriculture Technical and Vocational Education Training College Establishment, Council of Regional Government Regulation No.47/2006."

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. "የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና" ማለት በመደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ የአሰለጣጠን ስልት በተወሰነ የጊዜ እርዝማኔ በቅድመ ሥራ ወይም በሥራ ላይ ሥልጠና መርሃ ግብር የሚሰጥና እስከ ዲፕሎማ ደረጃ ያለው ማስረጃ የሚያስገኝ ትምህርት ወይም ሥልጠና ነው፤
2. "የአካዳሚክ ሠራተኛ" ማለት ከማስተማር፣ ከምርምርና ከስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ተግባር ጋር በተያያዘ ሥራ የተሰማራ ማናቸው የኮሌጁ ሠራተኛ ነው፤

### 2. Definition

Unless the context otherwise requires, in this regulation:-

1. "Agriculture and Technical Vocational Education and Training" means an Education or Training which is given in a formal or non-formal training method in pre-service or in-service training programs for different lengths of time so as to enable one to obtain a certificate up to diploma level.
2. "Academic employee" means any employee of the college who is engaged in teaching, research and curricular preparation activities related thereto.

www.abyssinialaw.com



3. “የአስተዳደር ሠራተኛ” ማለት የአካዳሚክ ሠራተኛ ያልሆነ የኮሌጁ ሠራተኛ ነው፤

4. “ቢሮ” ማለት የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ነው።

3. “Administrative employee” means an employee of the college who is not a member of the academic staff.

4. “Bureau” means the Amhara National Regional State Agriculture and Rural Development Bureau.

## ክፍል ሁለት
## ስለ ኮምቦልቻ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ መቋቋም፣ ዓላማ፣ ሥልጣንና ድርጅታዊ አቋም

## PART TWO
## ESTABLISHMENT, OBJECTIVE, POWERS AND ORGANIZATIONAL STRUCTURE OF COMBOLCHA AGRICULTURE TECHNICAL VOCATIONAL EDUCATION AND TRAINING COLLEGE

### 3. መቋቋምና ተጠሪነት

1. የኮምቦልቻ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ /ከዚህ በኋላ “ኮሌጁ” እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ ከፍተኛ የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

2. የኮሌጁ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል።

### 3. Establishment and Accountability

1. The Combolcha Agriculture Technical Vocational Training College,/hereinafter referred to as “The College”/ is hereby established under this regulation as an autonomous higher education and training institution of the regional state having its own legal personality.

2. The accountability of the college shall be to the Bureau.

### 4. ዓላማ

የኮሌጁ ዋና አላማ የግብርና ሳይንስን ከየአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ የሚሰሩ፣ በሙያው በቂ እውቀትና ክህሎት ያላቸው፣ በሚዛናዊ አመለካከትና በመልካም ስነ-ምግባር የታነፁ፣ ሥራ ወዳድ ዜጎችን በመፍጠር የክልሉን ማህበራዊና

### 4. Objective

The main objective of the college shall be to produce a trained human resource capable of realizing the socio-economic development of the regional state as well as fight against poverty and backwardness by creating job-loving citizens who perform the science of agriculture by relating with their surroundings of natural conditions,

www.abyssinialaw.com



ኢኮኖሚያዊ ልማት ዕውን ሊያደርግ የሚችልና ድህነትንና ኋላቀርነትን የመዋጋት አቅም ያለው የሰለጠነ ሰብዓዊ ሃብት ማፍራት ይሆናል።

professionally qualified and have adequate knowledge and skills, equipped with a judicious outlook and good ethics.

## 5. መደበኛ አድራሻ

የኮሌጁ መደበኛ አድራሻ በደቡብ ወሎ ዞን በኮምቦልቻ ከተማ ይሆናል።

## 5. Address

The address of the College shall be the town of Combolcha in South Wollo Zone.

## 6. የኮሌጁ ሥልጣንና ተግባር

ኮሌጁ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ዝርዝር መርሃ ግብሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ በክልሉ ውስጥ የግብርናና ገጠር ልማት ሙያተኞችን ያሰለጥናል፣
2. የተመዘገቡባቸውን የትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብሮች ላጠናቀቁ ሰልጣኞች እንደ አግባብነቱ ዲፕሎማ ወይም ሰርቲፊኬት ይሰጣል፣
3. የክልሉን ፍላጐት መሠረት ያደረጉ ሴሚናሮችን፣ አጫጭር ሥልጠናዎችንና ወርክሾፖችን ያዘጋጃል፣ ያካሂዳል፣
4. የተግባራዊ ልምምድ ፕሮግራሞችን ይመራል፣ ያስተባብራል፣
5. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተገቢውን ዋጋ ያስከፍላል፣ በዓላማው ላይ ተመስርቶ የውስጥ ገቢውን በየጊዜው ያዳብራል፣
6. ለኮሌጁ የሚያገለግሉ የመማሪያ መጽሐፍትን፣ መጽሔቶችንና ጆርናሎችን ያዘጋጃል፣ ያሳትማል፣ ለተጠቃሚዎች ያሠራጫል፣
7. በተለያዩ የግብርና መስኮች ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ለማፍራት የሚያስችሉና አገር አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የትምህርት፣

## 6. Powers and Duties of the College

The college shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. Train professionals of agriculture and rural developments in the regional state, its detailed program shall to be determined by a directive;
2. Award certificates or diplomas, as the case may be appropriate, to those trainees upon completion of the education and training programs for which they have been registered;
3. Organize and undertake seminars, short term trainings and workshops based on the needs of the Regional State;
4. Direct and coordinate programs of apprenticeship;
5. Collect charges for the services it renders and thereby increase its internal revenue based on its objectives;
6. Prepare and have published textbooks, magazines and journals to the service of the college as well as distribute them to the beneficiaries;
7. Formulate educations training and research programs maintaining their National standards with the view to enabling the college to

www.abyssinialaw.com



የሥልጠናና የምርምር መርሃ ግብሮችን ይቀርፃል፣ በቢሮው ሲፀድቁም በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

8. የአሰለጣጠን ስርዓቱ ግልፅ፣ ቀልጣፋና ፍትሃዊ ይሆን ዘንድ ሠልጣኞች የአካዳሚክና የአስተዳደር ሠራተኞችን የሚገመግሙበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤

9. በግብርናው ሴክተር ከሚሰሩ ድርጅቶች፣ ተቋማትና የግል ባለሃብቶች እንዲሁም ከሲቪል ማህበረሰቦች ጋር የጠበቀ የሥራ ግንኙነት ይፈጥራል፤

10. የራሱን የሥራ ዕቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ያዘጋጃል፣ የተፈቀደለትን የሰው ሃይል ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

11. በህግ መሠረት ውሎችን ይዋዋላል፣ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

12. አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

## 7. የኮሌጁ ድርጅታዊ አቋም

ኮሌጁ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 6 ስር የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ለማከናወን ይቻለው ዘንድ /ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" እየተባለ በሚጠራ/ አካዳሚክ ኮሚሽን የሚመራ ሲሆን የዕለት ከዕለት ሥራዎቹን የሚፈፅመው በዲኑ፣ በምክትል ዲኖቹና በትምህርት ክፍሎቹ አማካኝነት ይሆናል።

## 8. ስለ አካዳሚክ ኮሚሽኑ ምስረታ፣ ተዋፅኦና ተግባር

1. የኮሌጁ አካዳሚክ ኮሚሽን በዚህ ደንብ

produce efficient professionals in various agricultural fields thereof and cause the implementation upon approval of the Bureau;

8. Put into place and effectuate a system of evaluation of the academic and administrative staff by the trainees with the view to making the training system transparent, efficient and just:

9. Create strong working relationships with enterprises, institutions and private investors as well as civil communities engaged in the agricultural sector;

10. Prepare its own action plan and executionary budget, manage and administer manpower allocated to it;

11. Enter into contracts, own properties, as well as sue and be sued on its name, in accordance to law;

12. Perform such other related functions as may be helpful to accomplish its objectives.

## 7. Organizational stand of the College

The College shall, in order to accomplish its duties and responsibilities given to it under art.6 herein above, be directed by/ hereinafter referred to as "Commission"/ academic commission and its day-today activities shall be performed by the dean, the vice deans and the departments.

## 8. Establishment, composition and Duties of the Academic Commission

1. The academic commission of the college shall, pursuant to this regulation, be established on

www.abyssinialaw.com



መሠረት ከሚከተሉት ተውጣጥቶ ይቋቋማል፡-

ሀ/ የኮሌጁ ዲን ………………….. ሰብሳቢ

ለ/ የኮሌጁ ምክትል ዲኖች …….. አባላት

ሐ/ የትምህርትና ምርምር ክፍሎች ኃላፊዎች ………………………………. አባላት

መ/ የኮሌጁ ሬጂስትራር ጽ/ቤት ኃላፊ … አባል

ሠ/ የቤተ መጽሐፍትና ዶክመንቴሽን አገልግሎት ኃላፊ ……………………. አባል

ረ/ የተማሪዎች ጉዳይ አገልግሎት ኃላፊ ……………………………………….. አባል

ሰ/ አንዷ ሴት የምትሆንበት ሁለት የኮሌጁ መምህራን ተወካዮች ……………. አባላት

ሸ/ አንዷ ሴት የምትሆንበት ሁለት የኮሌጁ የተማሪዎች ተወካዮች …………… አባላት

2. ኮሚሽኑ ከአባላቱ መካከል አንዱን መረጠ በቃለ-ጉባዔ ፀሐፊነት ያሠራል።

3. የአካዳሚክ ሠራተኞች በኮሚሽኑ ውስጥ የሚኖራቸው የውክልና ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል። ሆኖም ለአንድ ጊዜ ብቻ እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ።

## 9. ስለ ኮሚሽኑ የስብሰባ ጊዜና የውሳኔ አሰጣጥ ስነ-ሥርዓት

1. ኮሚሽኑ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባውን ያካሂዳል። ሆኖም ይህ ድንጋጌ በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ከኮሚሽኑ አባላት መካከል አንድ ሶስተኛ በሚሆኑት ጥያቄ አቅራቢነት አስቸኳይ ስብሰባዎችን ከማድረግ የሚያግድ አይሆንም፤

2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የኮሚሽኑ አባላት

the composition of the following:

a. The dean of the college ……..… chair person;

b. The vice deans of the college ……. members;

c. The heads of departments research departments ……………………………….……. members;

d. Head of registrar of the college ….... member;

e. Head of library and documentation service …………………………………….. member;

f. Head of students' affair service …… members;

g. Two representatives of the college instructors, one of them is female ………….… members;

h. Two representatives, one is female, of the college students …………….…. members;

2. The commission selects one among the members and assigns secretary of minutes;

3. Term of representation of academic staffs shall be two years. Provided, however, that they may be re-elected only for one time.

## 9. Meeting Time and Decision-making Procedures of the Commission

1. The Commission shall carry out its ordinary meetings once a month. Provided, however, that this stipulation shall not prohibit extraordinary meetings from to be held either upon the call of the chair-person or the request submitted by one-third of the members of the commission.

2. There shall be a quorum when more than half of

www.abyssinialaw.com



በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤

the members show up at the meeting.

3. በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑትን የአብላጫ ድምፅ ድጋፍ ያገኘ ማናቸውም ጉዳይ የኮሚሽኑ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል። ሆኖም ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ወገን ሃሳብ የኮሚሽኑ ውሳኔ ይሆናል፤

3. All matters having won support of more than half of those members present at the meeting with majority vote shall pass to be the decision of the commission; provided, however, that, in case of a lie, the notion supported by the chair person shall be the decision of the commission;

4. ኮሚሽኑ በየጊዜው በሚያካሂዳቸው ስብሰባዎች በአስረጅነት የሚፈልጋቸውን ሰዎች ሊጠራና ሊያሳትፍ ይችላል። ሆኖም አስረጅዎች በማናቸውም ጉዳይ ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፤

4. The commission may convene persons, in an expert, to attend its meetings may be held at any time. Provided, however, that those persons shall not have the right to cast a vote at any matter.

5. ቀድሞ በኮሚሽኑ የተላለፈን ውሳኔ መሻርና በሌላ መተካት የሚቻለው ይህንኑ አስመልክቶ የቀረበው ጥያቄ ከአባላቱ መካከል በሁለት ሦስተኛው ድምፅ ሲደገፍ ብቻ ይሆናል፤

5. The decision passed by the commission earlier may be annulled and replaced by another one upon support of two-third vote of its members on the request concerning hereto.

6. ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚሽኑ ዝርዝር የስብሰባና ውስጣዊ የአሠራር ስነ-ሥርዓት ማስፈፀሚ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

6. Without prejudice to the provisions of hereinabove sub Art.1-5 of this art. hereof, the commission may issue specific meeting and internal working procedure implementation guideline.

## 10. የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

## 10. Powers and Duties of the Commission

The commission shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. በኮሌጁ የሚሰጠው ትምህርትና ሥልጠና በክልሉ ውስጥ በግብርናው መስክ የሚታየውን በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሃይል ችግር በሚቀርፍ አግባብ መደራጀቱን ያረጋግጣል፤

1. Ascertain that the education and training of the college is properly organized with the view to solving the problem of middle-level trained man power of the agricultural sector in the regional state;

www.abyssinialaw.com



2. በኮሌጁ የሚካሄዱት የምርምር ተግባራት የገበሬውን ዕውቀት የሚያዳብሩበትና ሙያተኛው ተፈላጊውን ዕውቀት የሚያስተላልፍበት አመች ስልት መቀየሱን ይከታተላል፣
3. በኮሌጁ የሚዘጋጀውን ካሪኩለም ረቂቅ መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለቢሮው ያቀርባል፣
4. ቢሮው የሚያዘጋጀውን ስርዓተ-ትምህርት መሠረት በማድረግ የኮሌጁ ትምህርትና ሥልጠና በአግባቡ መሰጠቱን ይገመግማል፣
5. የመማር ማስተማር ዘዴው የሚሻሻልበትን ስልት ይቀይሳል፣
6. የፈተና አሰጣጥ ዘዴዎችን፣ የተማሪዎችን የፈተና ውጤቶች አያያዝና የደረጃ ሽግግር በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፣ በቢሮው ሲፀድቅለትም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
7. የኮሌጁ መካነ ምርምሮችና ሌሎች መሰል ተቋማት ስለሚቋቋሙበትና ስለሚመሩበት ሁኔታ ይመክራል፣ ይወስናል፣
8. ኮሌጁ ከሃገር ውስጥና ከውጭ አገር ከፍተኛ የትምህርትና የማሰልጠኛ ተቋማት ጋር በሚኖሩት ግንኙቶች ላይ ይመክራል፣ ይወስናል፣
9. ወደ ኮሌጁ የሚገቡ ተማሪዎች ተገቢ የሆነ የትምህርት ማስረጃ ስለማቅረባቸው በሬጅስትራር ጽ/ቤት በኩል ምርመራ መካሄዱን ያረጋግጣል፣
10. ዝርዝሩ በመመሪያ የሚገለጽ ሆኖ በኮሌጁ ተማሪዎች ላይ የተወሰደ ከፍተኛ የዲስፕሊን

2. Follow up a suitable mechanism is devised for the research activities to be conducted in the college through which the knowledge of the farmer to be increased and the professional may transfer the desired knowledge to the farmers;
3. Examine the curriculum proposal prepared by the college, and submit same to the Bureau with recommendation;
4. Evaluate the education and training of the college to be properly given, in accordance with curriculum may be prepared by the Bureau;
5. Devise a mechanism by which the learning-teaching methods to be improved;
6. Issue guidelines with regard to the methods of administering exams, records of exam results of the students and a promotion system; cause its implementation up on approval of the Bureau;
7. Consult and decide up on the conditions by which research-sites and other related institutions of the college may be established and directed;
8. Consult and decide up on the relationships of the college with domestic and foreign higher educational and training institutions;
9. Ensure that an investigation is carried out through the office of registrar that students admitted to the college submit valid educational certificate;
10. With the details to be outlined by a directive, examine and give final decision where there is

www.abyssinialaw.com



እርምጃ ቢኖር በተማሪው በኩል ይግባኝ የተባለበት እንደሆነ ይህንኑ መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

11. የኮሌጁ ተማሪዎችና ሠራተኞች ደህንነት መጠበቁን ያረጋግጣል፤

12. ስለኮሌጁ ሥራ ማስኬጃ በሚዘጋጀውና በሚፈቀደው ረቂቅ በጀት ላይ በመወያየት ለየሥራ ክፍሎቹ የተደረገውን ጊዜያዊ የበጀት ድልድል ያፀድቃል፤

13. የውል አገልግሎት በተሻለ መንገድ ይሰጥ ዘንድ ቢሮው የሚያወጣቸው መመሪያዎች በኮሌጁ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤

14. ከቢሮው በሚሰጠው የሥልጣን ውክልና መሠረት የኮሌጁ የአካዳሚክና የአስተዳደር ሠራተኞች የደረጃ እድገት ሥርዓት ተፈፃሚ መሆኑን ያረጋግጣል።

## 11. ስለውሳኔዎች አፈፃፀም

1. የኮሚሽኑ ውሳኔዎች በዲኑ ጽ/ቤት አማካኝነት ይፈፀማሉ፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም በቢሮው መፈፀም ያለባቸው የኮሚሽኑ ውሳኔዎች በኮሌጁ ዲን አቅራቢነት ወደ ቢሮው ተላልፈው በሥራ ላይ ይውላሉ።

## 12. ስለኮሌጁ ዲን አሿሿምና ተጠሪነት

1. የኮሌጁ ዲን በቢሮው አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሾማል፤

grave disciplinary measures against students of the college and an appeal is made by the student;

11. Ensure that the security and well-being of students and employees of the college is safeguarded;

12. Discuss about budget proposal to be prepared and approved for the working capital of the college thereof and approve temporarily budget allocation for each divisions;

13. Follow up the implementation of directives in the college to be issued by the Bureau with the view to outsourcing a contractual service in an improved way;

14. Ensure the implementation of upgrading system of the academic and administrative employees of the college pursuant to the delegation of authority vested to it by the Bureau.

## 11. Execution of Decisions

1. Decision of the commission shall be implemented through the office of the dean.
2. Notwithstanding the provision of sub.Art.1 of this art. hereof, the decisions of the commission which may be executed by the Bureau shall be put into effect up on the submission to the Bureau by the dean of the college.

## 12. Appointment and Accountability of the Dean of the College

1. The college dean shall be appointed by the head of the Regional Government up on his presentation by the Bureau.

www.abyssinialaw.com



2. የዲኑ ተጠሪነት ለቢሮው ነው።

## 13. ስለዲኑ ሥልጣንና ተግባር

የኮሌጁ ዲን በዚህ ደንብ መሠረት የኮሌጁ ዋና ተጠሪ በመሆን የሚያገለግል ሲሆን ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የኮሌጁን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ ዕቅድና ረቂቅ የማስፈፀሚያ በጀት አዘጋጅቶ ለኮሚሽኑ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ለቢሮው ያስተላልፋል፤
2. ኮሚሽኑና ሌሎች የበላይ አባላት ያሳለፏቸውን ውሳኔዎች ተግባራዊነት ይከታተላል፣ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፤
3. ለኮሌጁ የተፈቀደውን በጀትና የተመደበውን የሰው ሃይል ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤
4. የኮሌጁን ሠራተኞች ቅጥርና የደረጃ ዕድገት እንዲሁም በዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት የሚወሰድባቸው እርምጃ በህግ መሠረት መከናወኑን በመመርመርና በማረጋገጥ ያፀድቃል፣ ከስልጣኑ በላይ ሆነው ያገኛቸውን ጉዳዮች ደግሞ ከተገቢው የውሳኔ ሃሳብ ጋር ለቢሮው ያስተላልፋል፤
5. የኮሌጁ ገንዘብና ንብረት በተገቢው መንገድ መያዙንና ለታለመለት አለማ መዋሉን ያረጋግጣል፤
6. በእቅድ አፈፃፀምና በበጀት አጠቃቀም ረገድ የሚገጥሙትን ችግሮች በወቅቱ በመገምገም ለኮሚሽኑ አቅርቦ ያስወስናል፤

2. The accountability of the dean shall be to the Bureau.

## 13. Powers and Duties of the Dean

Pursuant to this regulation, being as a chief representative of the college, the dean of the college shall have the following specific powers and duties:

1. Prepare short, medium and long-term, action plan and executionary budget proposal of the college, submit it to the commission and transfer same to the Bureau upon approval;
2. Follow up the application of decisions passed by the commission and other superior bodies thereof and supervise over their implementation;
3. Administer and supervise the approved budget and the manpower assigned to the college;
4. Approve by examining and ascertaining the recruitment and grade promotion of the employees of the college as well as disciplinary measures taken against them to be carried out in accordance with a law, and pass matters which are beyond his authority to the Bureau with appropriate recommendation;
5. Ensure that the finance and property of the college is properly handled and utilized for its intended purpose;
6. Evaluate timely and have determined problems encounted with regard to the performance of plan and utilization of budget upon submission to the commission;

www.abyssinialaw.com



7. ወደ ኮሌጁ የሚገቡትን ተማሪዎች ድልድል ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
8. የኮሌጁን አጠቃላይ አስተዳደር በበላይነት ይመራል፤
9. የኮሌጁን የሥራ እንቅስቃሴ የሚመለከት ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ለቢሮው ያቀርባል፤
10. ከቢሮው የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

## 14. ስለምክትል ዲኖች አሿሿምና ተጠሪነት

1. ኮሌጁ በቢሮው አቅራቢነት በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾሙ ሆነው የአካዳሚክና የአስተዳደር ዘርፎችን በበላይነት የሚመሩ ሁለት ምክትል ዲኖች ይኖሩታል፤
2. የምክትል ዲኖች ተጠሪነት ለዲኑ ይሆናል።

## 15. የአካዳሚክ ምክትል ዲን ሥልጣንና ተግባር

የኮሌጁ ምክትል የአካዳሚ ዲን ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የአካዳሚክ ጉዳዮችን በሚመለከት ዲኑን ያማክራል፣ በቅርብ ይረዳል፤
2. ኮሌጁ የሚሰጣቸው ሥልጠናዎች ኮሚሽኑ ባፀደቀው የትምህርት ካሌንደር መሠረት መካሄዳቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤
3. የትምህርቱን ሂደት ለማቀላጠፍ አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶችና አገልግሎቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

7. Follow up and supervise over the assignment of those students to the college;
8. Oversee the general administration of the college;
9. Submit quarterly report to the Bureau, concerning activities of the college;
10. Perform such other related duties may be given to him by the Bureau.

## 14. Appointment and Accountability of the Vice Deans

1. The college shall have two vice deans, appointed by Head of Regional Government upon their representation by the Bureau and thereby duty-bound to oversee the academic and administrative sections;
2. The vice deans shall be accountable to the Dean.

## 15. Powers and Duties of Academic Vice Dean

The academic vice dean of the college shall have the following powers and duties:

1. Advise and assist closely the dean concerning academic matters;
2. Follow up and ensure that the training activities of the college are carried out in compliance with the academic calendar adopted by commission;
3. Cause the fulfillment of supplies and services necessary for the facilitation of the education process;

www.abyssinialaw.com



4. የአካዳሚክ ሠራተኞች በተለያዩ የሥልጠና መስኮች የሚያዘጋጇቸውን አጫጭር የሥልጠና ሞጁሎችና የማስተማሪያ መጽሐፍት ዝግጅት ሂደት በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
5. የኮሌጁን የትምህርትና ሥልጠና ነክ ሥራዎች ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል።
6. የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞችን በየትምህርት ዘመኑ የጊዜ ሰሌዳ ከፋፍሎ በማውጣት ይነድፋል፣ እነዚህኑ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገው የሰው ሃይል፣ የማቴሪልና የአስተዳደር ድጋፍ የተሟላ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ይከታተላል፤
7. የኮሌጁን የጥናትና ምርምር ሥራዎች በኃላፊነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ የኮሌጁ መምህራንና ተማሪዎች በጥናትና ምርምር ተግባር የሚሳተፉበትን መንገድ ይቀይሳል፣ በዚሁ መስክ ከተሰማሩና አግባብነት ካላቸው ድርጅቶችና ተቋማት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣ የልምድና የተሞክሮ ልውውጦችን ያደርጋል፤
8. የኮሌጁ ቤተ-መጽሐፍትና ዶክመንቴሽን አገልግሎት ለመምህራንና ተማሪዎች በሚያገለግሉ አስፈላጊ መጽሐፍትና ሌሎች ግብዓቶች መሟላቱን፣ መደራጀቱንና ተገቢ አገልግሎት መስጠቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
9. የኮሌጁ ተማሪዎች በተቋሙ ውስጥ በሚደረገው የተግባራዊ ልምምድ እንቅስቃሴ እየተሳተፉ ወይም በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት

4. Oversee and supervise the preparatory process of short-term training modules and text-books prepared by the academic staff in various training streams;
5. Plan, organize, direct, coordinate and supervise education and training related activities of the college;
6. Schedule and devise programs of education and training in each academic year; ensure and follow up that the necessary manpower, materials and administrative support are fulfilled with the view to implementing hereof;
7. Direct and coordinate activities of study and research of the college, devise ways by which teachers and students of the college may participate in study and research activity, create relationships with pertinent organizations and institutions engaged in this field hereof and undertake experience and practicum sharings;
8. Follow up and supervise the library and documentation service of the college is furnished and organized with necessary books and other inputs to serve teachers and students and render appropriate service;
9. In consultation with pertinent bodies, launch programs whereby students of the college undertake apprenticeship in governmental and non governmental organizations and institutions

www.abyssinialaw.com



እየተገኙ የሥራ ልምምድ የሚያካሂዱበትን ፕሮግራም ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይዘረጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

or participate in the activities of practicum to be carried out in the institution and ensure its implementation;

10. ከየትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ጋር በመወያየትና የመምህራንን አስተያየት በመቀበል ተቋሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚሻሻልበትን መንገድ በመቀየስ የተቋሙን ኃላፊ ያማክራል፤

10. Advise head of the institution by devising ways whereby the institution to be improved from time to time through discussion with department heads and having received opinions of teachers;

11. ከየትምህርት ክፍሎቹና ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር የትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራሞችን፣ በጀትና የሰው ሃይል ዕቅድ ያዘጋጃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

11. In consultation with each heads of department and concerned bodies, prepare programs of education and training and plan of budget and manpower and follow up it implementation;

12. በእያንዳንዱ የትምህርት ካሌንደር በወጣው ፕሮግራም መሠረት ትምህርቱ ወይም ሥልጠናው በወቅቱ ተጀምሮ በሚገባ መሄዱን ይቆጣጠራል፤

12. Supervise the education or the training being commenced on time and is properly carried out in accordance with the scheduled time table in each academic calendar;

13. በኮሌጁ ውስጥ የኮምፒዩተር ማዕከል እንዲቋቋም ያደርጋል፣ በኃላፊነት ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣ ለኮምፒዩተር ተጠቃሚዎች የሥራ ፕሮግራም ያዘጋጃል፤

13. Cause the set-up of computer center in the college; administer and supervise over the institution thereof. Schedule a working program to the beneficiaries of computer;

14. በኮሌጁ የቅጥርና የደረጃ ዕድገት ማስፈፀሚያ መመሪያ መሠረት የመምህራን ቅጥር በተመጣጠነ የሰው ኃይል መከናወኑንና እድገታቸው መጠበቁን ያረጋግጣል፤

14. Ensure that the recruitment of teachers accomplished with adequate number of manpower up on the recruitment and upgrading implementation guiding of the college and thereby their career structure is maintained accordingly;

15. የተማሪዎች የትምህርትና ሥልጠና ሪከርድና የፈተና ውጤት በሚገባና በተሟላ ሁኔታ መያዙንና ለሚመለከተው ክፍል በወቅቱ መተላለፉን ያረጋግጣል፤

15. Ensure that education and training, records and exam results of the students are kept in a proper and complete manner and transferred timely to the concerned section;

16. የተመደበላቸውን ትምህርት ወይም ሥልጠና

16. Cause the determination of the list of those

www.abyssinialaw.com



አጠናቀው የሚመረቁ ተማሪዎችን ዝርዝር ለኮሚሽኑ አቅርቦ ያስወስናል፤

17. ዲኑ በማይኖርበት ወይም መደበኛ ሥራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሠራል።

## 16. የአስተዳደርና ልማት ምክትል ዲን

የአስተዳደርና ልማት ምክትል ዲን ተጠሪነቱ ለዲኑ ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የኮሌጁን የአስተዳደርና ፋይናንስ እንዲሁም የልማትና የተማሪዎች አገልግሎት ሥራዎች ያቅዳል፣ ይሠራል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፤
2. በኮሌጁ ውስጥ የተሻሻለና ዘመናዊነት ያለው የአሠራር ሥርዓት ተቀርጾ በሥራ ላይ ይውል ዘንድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ይከታተላል፤
3. ከኮሌጁ ትምህርት ነክ የሥራ ዘርፎች በሚቀርበው ጥያቄ መሠረት ዝውውር፣ ስንብት፣ የደመወዝ ጭማሪ፣ የዲሲፕሊንና የመሳሰሉት ጉዳዮች አግባብ ባላቸው ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈፀማቸውን ይከታተላል፤
4. ለተማሪዎች አገልግሎት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች፣ መሣሪያዎችና ሌሎች መሠረታዊ ቁሳቁሶች በተገልጋዮች ጥያቄ መሠረት ተሟልተው መቅረባቸውን ያረጋግጣል፣ ይከታተላል፤

students who may have completed the education or training allocated to them to be graduated;

17. Act on behalf of the dean in his absence or under the circumstances where and when he is unable to perform his normal duties.

## 16. Administration and Development Vice Dean

Being accountable to the dean, the administration and development vice dean shall have the following powers and duties:

1. Plan, perform, coordinate and direct the administration and finance of the college as well as activities of developments and students' service;
2. Render and follow up the necessary support for the formulation of improved and modern working procedure in the college in order to be implemented;
3. Upon the request of academic working divisions follow up the recruitment, upgrading, transfer, dismissal, salary increment and disciplinary and such like matters of the teachers and administrative staffs are implemented in accordance with the pertinent laws, regulations and directives;
4. Ensure and follow up that goods, materials and other basic utensils necessary for the service of students are fully provided upon the request of service seekers;

www.abyssinialaw.com



5. የኮሌጁን ተማሪዎች አጠቃላይ ደህንነት፣ አኗኗር፣ አመጋገብና ጤንነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በበላይነትም ይመራል፤
6. ለኮሌጁ ልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች የተፈቀደው ዓመታዊ በጀት በወጣው ዕቅድና ፕሮግራም መሠረት ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፤
7. ከኮሌጁ ዲን በሚሰጠው የሥልጣን ውክልና መሠረት ለኮሌጁ የሥራ እንቅስቃሴ የሚያስፈልገው ገንዘብ ወጪ እንዲሆን ያደርጋል፣ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
8. የኮሌጁ ገንዘብና ንብረት በሚገባ መያዙንና ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ያረጋግጣል፣ ተጨማሪ የአገልግሎት መስጫ ሕንፃዎች፣ መሳሪያዎችና ሌሎች ፋሲሊቲዎች የሚሟሉበትን ሁኔታ እንደአስፈላጊነቱ እያጠና ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
9. የኮሌጁን የውስጥ ገቢ ለማዳበር የተነደፉ ፕሮጀክቶች ተገምግመው ሥራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ ይሰጣል፣ ተፈፃሚነታቸውንም ይከታተላል፤
10. በኮሌጁና በተገልጋዩ ሕብረተሰብ መካከል ጤናማና ቀልጣፋ የሥራ ግንኙነት እንዲኖር ይጥራል፣ የክፍሉን ሥራ ለማቀላጠፍና ውጤታማ ለማድረግ የሚረዱ የአሠራር ስልቶችና ማንዋሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤
11. ከሥራው ጋር ግንኙነት ባላቸው ስብሰባዎች፣ ሴሚናሮችና የምክክር አውደጥናቶች ላይ እንደ አስፈላጊነቱ ይሳተፋል፤

5. Follow up, supervise and direct superiorly the overall security, way of living, nourishment and health condition of students of the college;
6. Supervise and follow the implementation of annual budget approved to varies working sections of the college upon the prepared plan and program;
7. Cause the withdrawal of finance necessary for the activities of the college upon the delegation of authority vested to him by the college dean; follow up and supervise its implementation;
8. Ensure that the finance and property of the college is properly handled and utilized for its intended purpose, study and submit the condition by which additional service delivery buildings, materials and other facilities to be fulfilled, as deemed necessary, and implement upon approval;
9. Render support for the implementation of projects devised with the view to increasing the internal revenue of the college, up on their evaluation, and thereby follow up their implementation;
10. Strive for the existence of smooth and efficient working relationships among the college and service seeking society and cause the preparation of working mechanisms and manuals which assist to facilitate and to be effective the activities of his office department;
11. Participate, as deemed necessary, in the meetings, seminars and workshops related to the activity;

www.abyssinialaw.com



12. በዲኑ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

## 17. ስለ ኮሌጁ ሌሎች የአካዳሚክ ክፍል ኃላፊዎችና ሠራተኞች

የኮሌጁ ሌሎች የአካዳሚክ ክፍል ኃላፊዎችና ሠራተኞች ቅጥር፣ ምደባ፣ የሥራ ድርሻና መሰል ጉዳዮች እንደ አግባብነታቸው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ወይም በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት እየታዩ የሚወሰኑ ይሆናሉ።

# ክፍል ሦስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 18. ስለበጀት

የኮሌጁ ገቢ ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፡-

1. የክልሉ መንግስት የሚመድበው በጀት፣
2. ኮሌጁ የሚሰበስበው የአገልግሎት ክፍያና የምርት ሽያጭ፤
3. ሌሎች።

## 19. የሂሣብ መዛግብትና ኦዲት

1. ኮሌጁ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብና የንብረት መዛግብትን ይይዛል፤
2. የኮሌጁ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ወይም ቢሮው በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየጊዜው ይመረመራሉ።

12. Perform such other related duties may be given to him by the dean.

## 17. Other Academic Division Heads and Employees of the College

The recruitment, assignment, job description and other affairs of other academic division heads and employees of the college shall, as may be appropriate, be determined by the directive to be issued by the Bureau or pursuant to the regional state civil service law.

# PART THREE

# MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 18. Budget

The revenue of the college shall be obtained from the following sources:

1. The budget allocated by the Regional Government;
2. Service charges and product sales to be collected by the college;
3. Others.

## 19. Books of Account and Auditing

1. The college shall have keep books of account and records which are accurate and complete thereto.
2. The books of account and other financial as well as property related documents of the college shall be audited at any time by the Office of the Auditor General of the Regional State or other auditors designated by the

www.abyssinialaw.com



Bureau.

## 20. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 20. Inapplicable Laws

Any other regulation, directive or customary practice inconsistent with this regulation shall not apply to matters provided for in this regulation.

## 21. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

ይህ ኮሌጅ ከመቋቋሙ በፊት በፌዴራሉ መንግስት ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሥር በነበረበት ወቅት ያገኛቸው መብቶችና የተጣሉበት ግዴታዎች ሚኒስቴሩ ፈቅዶ ከቢሮው ጋር በተስማማበት መጠን በዚህ ደንብ ወደ ተቋቋመው ኮሌጅ ተላልፈዋል።

## 21. Transfer of Rights and Obligations

The rights endowed and obligations imposed to the college, when it was administered by the Ministry of Agriculture and Rural Development before the establishment of this college, are hereinafter transferred to the college established under this regulation hereof, to the extent that the Ministry approved and has consented with the Bureau thereby.

## 22. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ይህንን ደንብ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪዎች ሊያወጣ ይችላል።

## 22. Power to Issue Directives

The Bureau may issue directives necessary for the full implementation of this regulation.

## 23. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ጥቅምት 9 ቀን 1999 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልል

መስተዳድር ምክር ቤት

## 23. Effective Date

This regulation shall come in to force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar

This 19th day of October, 2006

Council of the Amhara National

Regional Government

www.abyssinialaw.com